# “በየትኛውም ሚዛን ከኢህአዴግ የተሻለ ልምድም፣ የሕዝብ ድጋፍም አለን የሚል እምነት አለን”- ዶ/ር መረራ ጉዲና

*ዶ/ር መረራ ጉዲና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ሊቀመንበር ናቸው፡፡ ከአራት ወራት በኋላ በሚካሄደው አገራዊ ምርጫ ዙሪያ ታምሩ ፅጌ እና ሰብለወንጌል ሀብታሙ አነጋግረዋቸዋል፡፡*

--------------------

***ሪፖርተር፡- ከአራት ወራት በኋላ ለሚካሄደው  ምርጫ የመድረክ አጀንዳ ምንድነው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ያንን ከመመለሴ በፊት መመለስ የምፈልገው ኢህአዴግ ለምን ምርጫ ብሎ ራሱንም የኢትዮጵያ ሕዝብንና እኛንም እንደሚያስጨንቅ አላውቅም፡፡ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ምድር እንዲካሄድ ፍላጐቱ ከሌለው መተው ይሻለው ነበር፡፡ ሕዝቡንም ያለ ምርጫ ለመግዛት፣ ሕዝቡም በሰላም ለመኖር የተሻለ ዕድል ሊኖረው ይችል ነበር፡፡ ምርጫ በሚል ወከባው፣ እንግልቱ፣ ለምርጫ የሚንቀሳቀሱትን ማሰሩ፣ በዓለም ላይ ያለውን ሁኔታ በተለያየ መልኩ እየተጠቀመ እያጨናገፈ ነው፡፡ ስለዚህ እንደኔ ሕዝብ ወደ ስቃይ ውስጥ ከመክተት፤ የመንግሥትን ሃብትና ንብረትን ከማጥፋት፤ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲና ሌሎቹ መሰሎች በሚኖሩበት መንገድ ቢኖር ይሻል ነበር፡፡ የእኔ አቋም ይህ ነው፡፡*

*አንተ ላነሳህልኝ ጥያቄ፤ ዋናው የመድረክ አጀንዳችን የኢህአዴግ መንግሥት ላለፉት 18 ዓመታት በብዙ መንገዶች በተለይም ሰላምና መረጋጋትን በማምጣት ከዚያም አልፎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልማትና ብልፅግናን ማምጣት አልተሳካለትም፡፡ ያልተሳካለትን መንግሥት ደግሞ ሕዝቡ በነፃና በፍትሐዊ መንገድ ከሥልጣን የማውረድ መብት አለው፡፡ ስለዚህ መድረክ እየተንቀሳቀሰ ያለው ያልተሳካለትን መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ከሥልጣን የሚያወርድበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እየባተለ ነው፡፡ ዋናው ዓላማው በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ፖሊሲው በማንኛውም መንገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያልሆነለትን መንግሥት ከሥልጣን ለማውረድ የሚያደርገው ዋናው አጀንዳው ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የቆመ አጀንዳ አለው፡፡ አንደኛው፣ በኢትዮጵያ ምድር ሰላምና መረጋጋት ለመፍጠር ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በሰላም የሚንቀሳቀሱበት፣ ሕዝቡ በሰላም ሰርቶ የሚኖርበትና የሚገባበት፣ ከካድሬዎች ወከባና ከእንግልት የሚድንበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡*

*ሁለተኛው አጀንዳችን በኢትዮጵያ ምድር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ካልተፈጠረ በቀር ሁላችንንም በእኩልነት ሊያስተናግድ የሚችል ሰላምና መረጋጋት፣ የተሻለ ልማትና ብልፅግና ሊመጣ አይችልም፡፡ አምባገነን ስርዓትን እያሰፈነ ያለውን የኢህአዴግ መንግሥት አስወግዶ ሁላችንንም በእኩልነት ሊያስተናግድ የሚችል ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት ማምጣትና ሃቀኛ የፌዴራል ስርዓት በኢትዮጵያ ለመፍጠር እንንቀሳቀሳለን፡፡ ሦስተኛው አጀንዳችን፣ ልማትና ብልፅግና በዚህ አገር እየመጣ አይደለም፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በየዓመቱ እየተራበ ነው፡፡ ከዓለም ሕዝቦች ምፅዋት እየለመንን የምንኖርበት ይህ የአንድ ወይም የሁለት ዓመታት ሳይሆን ባለፉት መንግሥታትም የነበረ ሁኔታ ነው፡፡ በኢህአዴግ መንግሥትም እየተባባሰ፣ የኑሮ ውድነቱ ተራው ሕዝብ ሰርቶ የማይበላበትና የሕዝቡ ሕይወት ምስቅልቅ ነገር ውስጥ የገባበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ኢህአዴግ ጠዋትና ማታ ገጠሩን ማዕከል ያደረገ የሚለው ከመፈክር ያላለፈው የልማት ስትራቴጂ ተለውጦ፤ ከተማውንም ገጠሩንም አንዱ ሌላውን እያገዘ እኩልነትና ሚዛን የጠበቀ ስርዓት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ እራሱ መብላት ያልቻለ ገበሬ፣ ከራሱ ተርፎ ለከተማው ይተርፋል ማለት ተረት ነው፡፡ ኢህአዴግም ከልቡ ላለፉት 18 ዓመታት የሆነውን የሚያውቅ ይመስለኛል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን የተዛባ የኢኮኖሚ ስርዓትን ለውጦ ተራው ዜጋ ዳቦ በልቶ ሊኖርበት የሚችልበትን ልማትና ብልፅግና በኢትዮጵያ ምድር እንዲመጣ መድረክ ይንቀሳቀሳል፡፡ እኛ በእነዚህ ሦስቱ ምሰሶዎች ላይ የተመሠረትንና 65 ገፅ መለስተኛ ፕሮግራም ወይም ማኒፌስቶ ያወጣን ሲሆን፣ ከማኒፌስቶው ወደ 35 ገፅ የሚጠጉ ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዙ ናቸው፡፡ በትምህርት፣ በጤና፣ በማኅበራዊ ጉዳይ፣ በሰብዓዊ መብት … መሠረታዊ ጉዳዮችን ያካተቱ ናቸው፡፡*

*ሰላምና መረጋጋት የመፍጠሩ፣ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የመፍጠሩ፣ ልማትና ብልፅግና የማምጣቱ ዋና ዋና የመድረክ አጀንዳዎቹ ናቸው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት ለ18 ዓመታት የገፋበትን የፖለቲካ ፕሮግራም አማራጭ የሆነ ፕሮግራም ነው የቀረፅነው፡፡*

***ሪፖርተር፡- የስምንት ፓርቲዎች ጥምር በሆነው መድረክ ውስጥ የተለያዩ ርእዮተዓለም የሚያራምዱ የፓርቲ መሪዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ከፊሎቹ ሊብራል ዴሞክራሲ፣ ከፊሎቹ ሶሻል ዴሞክራሲ … ፖለቲካ አራማጆች ናቸውም ይባላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተስማምቶ መቀጠል ይቻላል ይላሉ?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ይህ ነገር አዲስ አይደለም፡፡ የተለያየ የፖለቲካም ሆነ የርዕዮተዓለም አመለካከት ያላቸው በተለያዩ አገራትም አሉ፡፡ የተሻለ ልማትና ብልፅግና ለማምጣት፣ ብሔራዊ የአንድነት መንግሥት ለመፍጠር ወይም ፓርቲዎች በቂ ድምፅ ሲያጡ ጥምር መንግሥት ይፈጠራል፡፡ የአንድ ፓርቲ ሳይሆን የስምንት ፓርቲዎችንም መንግሥት እንፈጥራለን ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ጀርመን*

ገዢው ፓርቲ በጥምር መንግሥት ነው ያለፈው ሶሻል ዴሞክራቶች አሸንፈው መንግሥት ቢመሰርቱም፣ ከሶሻል ዴሞክራቶች ጋር የቀኝና የግራ ኃይሎች ጥምር ነበር፡፡ አሁን ደግሞ የተሻለ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሲያገኝ ከነሱ ጋር ሆኗል፡፡ በኢትዮጵያም ብቻ ሳይሆን የቆዩ እነ ፈረንሳይ፣ ኔዘርላንድ፣ ስዊድን ... ፈጥረው ያውቃሉ፡፡ መጀመሪያ ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው ፓርቲ የሚቀርበውን ፓርቲ ይመርጣል፡፡ ሌላውም እንዲህ እንዲህ እያለ ከሌላው ጋር ጓደኝነት ይፈጥራል፡፡ የተለያየ አቋም ያላቸው ግን በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ከተስማሙ ሀገርን ለመምራት የማይችሉበት ምክንያት የለም፡፡ የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ በመሠረታዊ ጉዳዮች ኢትዮጵያን ምን እናድርጋት? እንዴት ወደፊት እንውሰዳት? እንዴት እንታደጋት? ከገባችበት ቀውስ እንዴት እናውጣት? ሰላምና መረጋጋት እንዴት እንፍጠር? ሁሉንም በእኩልነት ሊያስተናግድ የሚችል ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዴት እንፍጠር፣ ልማትና ብልፅግና እንዴት እናምጣ? የገጠርንና የከተማን ሚዛን የጠበቀ ዘመናዊ ኢኮኖሚና የግብርና ኢኮኖሚው እንዴት ተጣጥሞ ሥራ ላይ እንዲውል እናድርግ? ... ላይ ስምምነት አለን፡፡ ስምምነት የሌለን በተወሰኑ ነገሮች ላይ ነው፡፡ ልዩነቱ የማያሰራ ነገር አይደለም፡፡

***ሪፖርተር፡- ኤትኖ ናሽናሊዝምና ሲቪክ ናሽናሊዝም የሚባል ነገር አለ፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ መድረክ ምሁራን ሁለቱን ነገር መለየት ካልቻለ ችግር ይፈጠራል ይላሉ፡፡ የክልል ፓርቲዎች ናችሁና ይሄን ጉዳይ በጥልቀት ታይቷል ወይ? በእናንተ (በመድረክ) በኩል ስጋት ይፈጥራል?***

**ዶ/ር መራራ፡-** መድረክ እንዲፈርስ የሚፈልጉ ብዙ ናቸው፡፡ እነዚን ነገሮች አውቀን ከአንድ ዓመት በላይ ተደራድረን ነው የጀመርነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆኑ እናውቃቸዋለን፡፡ በኢትዮጵያ ሁኔታ ሁለቱም የሲቪክም፣ የዝርያ ብሔርተኝነትም ተጋግዘው ተጣጥመው ሚዛናቸውን ጠብቀው ካልሄዱ በስተቀር የአንዱ ብቻ መጫን አስቸጋሪ መሆኑ እንደማያዋጣ፣ ዜጎችን እንደሚጐዳ እናውቃለን፡፡ በነገራችን ላይ እናንተም እንደምታውቁት ኢህአዴግ አካባቢም ቀላል ያልሆነ ሚና ሲጫወቱ የነበሩ ሰዎች እኛጋ የመጡ አሉ፡፡ ኢህአዴግ ካምፕ ውስጥ ለ30 ዓመታት ምን ሲሰራ እንደነበር ስለሚያውቁ፤ አሁን ካሉት የኢህአዴግ መሪዎች ከብዙዎቹ የበለጠ የተጓዙበትን መንገድ የሚያውቁ ኃይሎች እኛ ጋ አሉ፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን ጀምሮ በተቃዋሚው ጐራ ደግሞ ብዙ ዓመታትን ያገለገሉ፣ ያካባቢውን ፖለቲካ የሚያውቁ አሉ፡፡ ህብረብሔርም ሆነው የተንቀሳቀሱ ኃይሎች አሉ፡፡ ያ ሁሉ ከልምድ ነው የሚመጣው፡፡ ኢህአዴግም ካምፕ ያለው ልምድ፣ ተቃዋሚ ጐራም ያለው ልምድ እዚህ መሃል ያሉትም ልምዶች አንድ ላይ ይዞ እንዴት ይችን ሀገር ሚዛኗን ጠብቀን ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በመተው የፈለገውን ፓርቲ ይምረጥነው ዋናው ጉዳይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍርድ እንቀበላለን ወይስ ኢህአዴግ አሁን እንደሚያደርገው "ሲበርድ በእጁ ሲፈጀው በማንኪያ" (ሲመቸው ዴሞክራት ነኝ ይላል፣ አልመች ሲለው ጠመንጃውን ያነሳል) ነው መሆን ያለበት? ... እንዲህ ዓይነት ነገር ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመቸንም አልተመቸንም ፍርዱን ለሕዝቡ መተው ነው፡፡ ባሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ፣ ባሉት የሀገሪቱ መሪዎች ላይ፣ ሕዝቡ እንዲወስንበት ማድረግ ነው፡፡ እነዚህን መሪዎች ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ፖሊሲዎች ይፈልጋሉ፣ የሚለው ላይ መስራት፤ እነዚህ ፖሊሲዎች ይጐዱኛል እነዚህ ፖሊሲዎች ጥቅሜን አላስከበሩልኝም የሚሉበት ስርዓት ካልፈተጠረ ሌላው የትም አያደርሰንም፡፡ ዋናው ጉዳይ እዛ ለመድረስ የየበኩላችንን አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ በየትኛውም ሚዛን ከኢህአዴግ የተሻለ ልምድም፣ የሕዝብ ድጋፍም አለን የሚል እምነት አለን ይህንን ሥራ ላይ ለማዋል፡፡

***ሪፖርተር፡- በምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ላይ ከኢህአዴግ ጋር ካልሆነ ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር አንዳራደርም ብላችኋል፤፡ ባለመደራደራችሁ ያገኛችሁት ጥቅም ምንድነው? ያጣችሁትስ?***

**ዶ/ር መራራ፡-** እኔ ያንን ያህል ጥቅሙንም ጉዳቱንም አላየሁኝም፡፡ ዋናው ጉዳይ ፈረንጆች የፃፉት "ኢንተርናሽናል አይዲያ" የሚባለውን ሦስት መሠረታዊ ሰነዶችን ነው ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ያዘጋጀው፡፡ አንደኛው፣ በሙያና በስነ ምግባር ላይ የተመሠረተ የምርጫ አስተዳደር፣ (ኤቲካል ኤንድ ፕሮፌሽናል አድሚኒስትሬሽን ኦፍ ኢሌክሽን) የሚል ሰነድ፤ ዋናውና ሁሉም ነገር የሚቆመው በዚህ ሰነድ ላይ ነው፡፡ ይህም ..የሕዝብ ድምፅን ማን ይቆጥራል.. የሚለው ነው፡፡ ገለልተኞች ናቸው ወይስ የአንድ ፓርቲ ጥቅም አስከባሪዎች ናቸው? ከአንድ ፓርቲ የተላኩ የአንድ ፓርቲ ጉዳይ አስፈፃሚዎች ናቸው ወይስ በሃቅና ነፃ ሆነው፣ ገለልተኛ ሆነው ሕዝቡን በእኩልነት የሚያስተናግዱ ናቸው የሚለውን የሚገልፅ ነው፡፡ ሁለተኛው ዋናው ሰነድ ታዛቢዎች የሚለው ነው፡፡ እነዚህ ታዛቢዎች አንድ ጨዋታ ላይ ተጫዋቾቹ በሜዳው ላይ በነፃነት ተጫውተዋል ወይ? የተዛባ ነገር አለ ወይ? በሃቅ ላይ የተመሠረተ ጨዋታ ተካሂዷል ወይ? ተጭበርብሯል ወይ? እነዚህ እነዚህ ነገሮችን የሚታዘቡ ናቸው፡፡ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መካሄድ አለመካሄዱን አይተው የሚፈርዱ ናቸው፡፡

ሦስተኛው የሥነ ምግባር ደንብ የሚባለው ነው፡፡ ይህ በእነዛ መሠረታዊ ሰነዶች ላይ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ከተደረገ እንደ ማሰሪያ ነው፡፡ እንዴት ሥራ ላይ እናውል? ምን እናድርግ የሚል ነው፡፡ ለምሳሌ በክርክር ጊዜ እንዴት እንፍታ፣ ምን ቢሆን ምን እናድርግ የሚለውን ማሰሪያ ነው እንጂ እነዛን የሚተካ አይደለም፡፡ ይህም ከሌሎቹ ጋር ከሆነ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ያለሁለቱ ከሆነ ግን ዋጋ ቢስ ነው፡፡ ከተፃፈበት ወረቀት ዋጋ በታች ይሆናል፡፡

ኢህአዴግ ግን እነዛን ሁለቱን መሠረታዊ ነገሮች አልፎ፣ ደብቆ፣ በሥነ ምግባር ደንቡ ላይ እንፈራረም ይላል፡፡ ማነው የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምፅ የሚቆጥረው? የሚለውን ይህ ሰነድ አልመለሰም፡፡ በማድበስበስ ብቻ ስለሱ በኋላ እንነጋገራለን ነው እንጂ ሌላ መልስ አይሰጥም፡፡ ከ200ሺ በላይ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ያሰማራው ኢህአዴግና የአካባቢው አስተዳደሮች ናቸው፡፡ በየትኛውም ፍርድ ቤት ለመርታት እንችላለን? ኢህአዴግ ካድሬዎችንና ደጋፊዎችን ማሰማራቱን ሚሊዮኖችን ምስክር መጥራት እንችላለን፡፡ እነዚህ 200ሺ

ዳኞችን (ምርጫ አስፈፃሚዎችን) አንድ ፓርቲ መልምሎ ካሰማራ፣ ያ ፓርቲ (ኢህአዴግ) ተጫዋችም፣ ዳኛም ነው፡፡ ብዙ ጣቢያዎች ላይ 11 ለ አንድ ነው የምንሆነው፡፡ አንድ ተቃዋሚ 11 የኢህአዴግ ደጋፊዎች፡፡ አምስት ምርጫ አስፈፃሚዎች አሉ፡፡ አምስት ታዛቢዎችን ደግሞ ተቃዋሚዎች በሌሉበት በኢትዮጵያ ምድር በሙሉ አስመርጧል፡፡ እነዚህ ደግሞ ከ200ሺ በላይ ናቸው፡፡ በዚህ ምርጫ ላይ ከ400ሺ በላይ ሰው የሚንቀሳቀሰው በአንድ ፓርቲ ነው፡፡ ባለው መንገድ በየትኛውም ሚዛን፣ (የስኬት ዘመን ምርጫ የሚባል አለ፡፡ ምርጫ ይባላል ግን ቅርጫትም አይሆንም) ኢህአዴግ ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ እንዳልተዘጋጀ አውቀን ነው እየገፋን ያለነው፡፡ አሁንም ቢሆን የኢህአዴግን መሪዎች ደጋግመን የምንጠይቀው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ውድድር እንዲካሄድ ከተፈለገ፣ መድረኩ ባቀረባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች፣ የሕግ የበላይነትን ጨምሮ፣ የምርጫ አስተዳደርን ጨምሮ፣ የታዛቢዎች ጉዳይን፣ የሚዲያ ጉዳይን፣ … በመሳሰሉት ላይ መደራደር አለብን ነው፡፡

***ሪፖርተር፡- ስነ ምግባር ደንቡ ፓርላማ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** የአገሪቱን ሕግ እናከብራለን፡፡ ስናከብር ግን ነፃና ሐቀኛ፣ ፍትሐዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ምድር መካሄድ እንደማይችል ለኢትዮጵያ ሕዝብ በመግለጽ፣ ለዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡ የመግለፅ ግዴታችን ነው፡፡ በእነደዚህ ዓይነት ጨዋታ የሶቪዬት ዘመን ምርጫ ነው የሚሆነው፡፡

***ሪፖርተር፡- የመራጮች ምዝገባ እየተካሄደ ነው፡፡ በቀጣይ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር ያደርጋሉ፡፡ ምርጫውን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ መድረክ ምን እያደረገ ይገኛል?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** እኛ ድርድሩ የተሳካ ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈለገውን ሊመርጥ የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ትግሉን መቀጠል ነው፡፡ ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ትግሉን ከመቀጠል ውጭ ምንም ምርጫ የለንም፡፡ ነገም ሊሆን ይችላል፣ ሌላም ጊዜ ሊሆን ይችላል ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ምድር እንዲካሄድ የኢህአዴግ መሪዎችን ደጋግመን እንጠይቃለን፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሕጋዊና ሰላማዊ ትግሉን ከእኛ ጋር እንዲቀጥል አስፈላጊውን ጥረት እናደርጋለን፡፡

***ሪፖርተር፡- በቅርቡ በሥነ ምግባር ደንቡ ላይ ተስማምተው የፈረሙ ፓርቲዎች ምክር ቤት አቋቁመዋል፡፡ በምክር ቤቱ ለመካተት ወይም በስነ ምግባር ደንቡ ላይ መስማማታቸውን ሊያሳውቁ ከመፈረማቸው በፊት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጠዋል፡፡ በዚህ ላይ የመድረክ አቋም ምንድን ነው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** እኛ እኮ እንገባ አላልንም፡፡ ቀደም ብዬ ያነሳሁት ነገር መፍትሔ ካልተሰጠው ገባን አልገባን ምን ትርጉም አለው? በተለይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምፅ የሚቆጥረው ማነው? ገለልተኛ የምርጫ አካል ነው? ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚዎች ወይስ ማን ነው? በሚለው ላይ ተደራድረን ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚዎች ማድረግ ስንችል ነው፡፡ እሱን ደግሞ ማድረግ አልቻልንም፡፡ ከዛ ውጭ ያለው ጨዋታ እኮ ዝም ብሎ ነው፡፡

***ሪፖርተር፡- ይህ ጥያቄ ካልተመለሰልን ወደ ምርጫም አንገባም እያሉኝ ነው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** ወደ ምርጫው አንገባም እንገባም ብለን አልወሰንም፡፡ በ11ኛው ሰዓትም የመውጣት መብት (ፖሲቢሊቲ) ስላለን፡፡ አሁን ግን ምርጫው ውስጥ እንገባለን ብለን ከልብ እየሠራን ነው፡፡ ያለንን አቅም ሁሉ በሥራ ላይ አውለን እየሠራን ነው፡፡ የኢህአዴግ ችግር ግን በአንድ በኩል በተለይ ወጣቶች፣ አስተማሪዎች፣ ጠቃሚ የፓርቲ ደጋፊዎች አባሎች እንዳይመዘገቡ በዓለም ላይ ያለውን ትራክ ሁሉ እየተጠቀመ እድሜህ ገና ነው፣ እንደዚህ ኣላደረክም … እያለ እያደናቀፈ ነው፡፡ ለምሳሌ የገጠመንን ለመግለፅ ያህል፤ ከአዲስ አበባ ወደ ወለጋ ስንሄድ "መውጫ አልያዝክም" በሚል መንጃ ፈቃድ ቀምተው ቅጣት ቀጡ፡፡ ተቀጥቶ ሲንቀሳቀስ (ሹፌሩ) በምንፈልገው አካባቢ ሲደርሱ የአካባቢው አስተዳደር "ምን ልትሰሩ ነው የመጣችሁት፣ ማለፍ አይቻልም" በሚል መልሷቸዋል፡፡ በአካባቢው ያሉትን አባሎቻችንን አስሯል፡ ሊያውም የፓርላማ አባላት፡፡ ምሥራቅ ወለጋ ውስጥ ዲጋአያና የሚባል ቦታ እየተንቀሳቀሱ፡፡ በአጠቃላይ አባሎቻችን እየታሰሩ ነው፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግረስ (ኦሕኮ) አባላት ከመስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ወዲህ ብቻ ከ150 በላይ አባላቱ ታስረዋል፡፡ ለምሳሌ ከነ አባዱላ ጋር የተወዳደሩት፣ ከሻትና ከሌላ ነገር ጋር በማገናኘት በማሰር ተፈርዶባቸው የሚገኙ አሉ፡፡

***ሪፖርተር፡- በሻኪሶ ወረዳ ጉጂ ዞን ለሚድሮክ ጐልድ ለልማት በተሰጠ ተጨማሪ መሬት ምክንያት ረብሻ በመነሳቱ በርካታ ሰዎች ታስረውና ተማሪዎች ትምህርት አቋርጠው ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ፓርቲዎች እጅ አለበት የሚሉ ወገኖች አሉ እርስዎ ምን ይላሉ?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** ስሙን መናገር የማልፈልገው የኦሮሚያ ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ሰው ከሁለት ዓመት በፊት ሚድሮክ ጐልድ ለወርቅ ማጠቢያ የሚጠቀምበት መርዝ የነዋሪዎችን ከብቶች እየገደለና ሕዝቡንም እየጐዳ መሆኑን ደጋግሞ ለምክር ቤቱ አባላት መናገሩን ነግሮኛል፡፡ ይህንን አለቆቹም ያውቃሉ፡፡ ችግሩ በቅርቡ የተነሳ አይደለም፡፡ ችግር እየሰፋ ሲሄድ ሕዝቡ በቃ

ማለት ጀመረ እንጂ የማንም ግፊት እንደሌለበት የክልሉ መንግሥትም ያውቃል፡፡ መረጃም አለው እኛም አለን፡፡ ሕዝቡ የኦሕዴድን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሰብስቦ አቤት ብሏል፡፡ ብሶት ሲበዛና ምላሽ ሲያጣ ሕዝቡ ሆ ብሎ ተነሳ፡፡ ከምርጫ 97 በፊት በክልሉ ሄጂ ከሃዋሳ የሦስት ሰዓት መንገድ ነበር፣ አሁን በቅርቡ ሄጄ ሰባት ሰዓት ፈጅቶብኛል፡፡

***ሪፖርተር፡- ለምን?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *መንገዱ የወርቅ ማዕድኑን ሊጭኑና ሊያጓጉዙ በሚመላለሱ ከባድ ተሽከርካሪዎች ከመቆፋፈሩ የተነሳ በግሬደር የታረሰ ይመስላል፡፡ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ (ልጆች እያለን) ዳሎል ወርቅ ሲባል እኛም እንሰማ ነበር፡፡ ወርቁ ይዛቃል እንጂ ሕዝቡ መንገዱን በሚመለከት ጥራት ያለው ውሃን በሚመለከት፣ ጤና ጣቢያን በሚመለከት ምንም ዓይነት ጥቅም እያገኘ አይደለም፡፡ እያነሳ ያለው ጥያቄም ይህንኑ ነው፡፡ በጣም የተጐዳና ከአካባቢው ወርቅ ሲታፈስ ለዘመናት የተመለከተ ሕዝብ መሆኑን የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናትም በቁጭት የሚመለከቱት ጉዳይ ለመሆኑ እኔም መረጃ አለኝ፡፡*

***ሪፖርተር፡- መድረክ ከሌሎቹ ፓርቲዎች ጋር (ከኢህአዴግ በስተቀር) መደራደር የማይፈልገው ለምንድነው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ብዙ ነገሮች ውስጥ ሳልገባ አሁን ሁለት ካምፕ ነው ያለው፡፡ ኢህአዴግና አጋሮቹ፣ መድረክና አጋሮቹ ናቸው ያሉት፡፡ ይህ ሰላምና መረጋጋት በስነ ሥርዓት የኢህአዴግና አጋሮቹ ባንድ ካምፕ (ጐራ) ሃቀኛ ተቃዋሚዎች የሚባሉት ደግሞ መድረክን ጨምሮ በሌላ ጐራ ያሰለፈ ነው፡፡ ዋና ጉዳይ ኢህአዴግ ስለሆነ ከሱ ጋር እንነጋገር እያልን ነው፡፡ እሱ ግን አልነጋገርም አለ፡፡ ዛሬም እየጠየቅን ነው፡፡*

***ሪፖርተር፡- ሌሎቹ ባሉበት እንደራደርም በማለታችሁ ነው ኢህአዴግ አልደራደርም ያለው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ይህ ይህ ትልቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ነው እንደዛ የሚያደርገው እኛ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ እንደራደር እያልን ነው፡፡ ኢህአዴግ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ መደራደር ስለማይፈልግ በብልጠት እየሸሸ ነው፡፡ ጨዋታው እዚያ ላይ ነው፡፡ እኛ እያልን ያለነው የሥነ ምግባር ደንብ ላይ በፈለጋችሁት ጊዜ ለመፈረም ዝግጁ ነን፡፡ ምንም ነገር ሳንደራደር ነገር ግን እነዛን መሠረታዊ ጉዳዮች ወስደን እንደራደር ነው የምንለው፡፡ በእነሱና በኛ መካከል ለሚመላለሱት ሽማግሌዎች በዚህ ላይ ተደራድረን ስንጨርስ በሁሉም ላይ እንፈርማለን ብለናቸዋል፡፡ እነሱ ግን እዚያ ላይ በቅድሚያ ካልፈረማችሁ በነዚህ ላይ አንደራደርም ነው ያሉት፡፡*

***ሪፖርተር፡- አደራደሪ ሽማግሌዎቹ እነማን ናቸው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ስም ምን ያደርግልሃል፡፡ ያሉትን ሽማግሌዎች ታውቃቸዋልህ፣ ቅንጅትን ያስፈቱ፣ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡*

***ሪፖርተር፡- አንድ የኢህአዴግ አባል "መድረክ ራሱ ጠፍቶ እኛም ይዞን እንዳይጠፋ" ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ በዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ኢህአዴግ መድረክን የፈራበት ምክንያት አለው፡፡ መድረክ ትንሽ ቀዳዳ ካገኘ የ97ቱን ያህልም ባይሆን ትንሽ ቀዳዳ ካገኘኢህአዴግ ግን በጠራራ ፀሐይ ያሸንፋል፡፡ ይህንን ኢህአዴግም ያውቃል፡፡ እኛ በዘጠኙም ክልሎች ማሸነፍ እያስፈልገንም፡፡ ኦሮሚያን ብንወስድ ትንሽ ቀዳዳ ከከፈትን (ኢህአዴግን) ማሸነፍ አያቅተንም፡፡ ደቡብና አማራ ክልል ለማሸነፍ ብዙ አያስቸግረንም፡፡ ኢህአዴግን ከሥልጣን ለማውረድ እነዚህ ክልሎች ብቻ ይበቁናል፡፡ ኢህአዴግ ግን ለማሸነፍ የሰውም ድጋፍ ተወዳዳሪዎችም አሉን፡፡ የሚያስፈልገን 274 መቀመጫ ቢሆንም ከ500 በላይ ዕጩ እናሰልፋለን፡፡ ግን ይህንን ለማድረግ ኦሮሚያንና አማራ ክልሎችን ብቻ ማሸነፍ በቂ ነው፡፡ ኢህአዴግ ትንሽ ፍትሐዊና ነፃ ምርጫ ካካሄደ ይሸነፋል፡፡ የያዘውን የሰው ኃይል እኮ እናውቃለን፡፡ ከሕዝቡ ጋ ያለውን ዝምድና (ቅርርብ) እናውቃለን፡፡ ካድሬው ሕዝቡን እንዴት እያመሰና እያዋከበ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ የ97ን ሁኔታ ሁላችንም እናስታውሳለን፡፡ ለምሳሌ ያህል ለማስታወስ ኢተያንና ሌሎች የኦሮሚያ ወረዳዎች ላይ የተቃዋሚ ተወዳዳሪዎች የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎችና ገበሬዎች ሆነው አቶ ጁነዲንና አቶ አባዱላን እንዴት እንዳሸነፏቸው አይተናል፡፡*

***ሪፖርተር፡- ዶ/ር መረራ በጭብጥ ላይ ከማተኮር ይልቅ በግለሰቦች ላይ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ ፌዝ ያበዛሉ የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ምላሽዎ ምንድነው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** *ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ጭብጡ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ፡፡ ሰዎች ደግሞ በፖለቲካ ጨዋታዎች ውስጥ እስካሉና ተዋናኝ እስከሆኑ ድረስ፣ ከጭብጡ ጋር አገናኝቶ የመናገር ሁኔታ አለ፡፡ ሁለቱን አገናኝቶ ማብራርያ መስጠት ካልተቻለ ደረቅ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ኢሕአዴግ ቆንጆ ፖሊሲ ሊኖረው ይችላል፡፡ ያንን ፖሊሲ ሊያስፈፅመው ካልቻለ ምንድነው? የሰበበሰበው ካድሬ ምን ይሰራል? መሪዎቹ እየመሩ ነው? ብለህ ትጠይቃለህ፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ፖሊሲ መጥፎም ጥሩም ነው፡፡ እኛ*

የምናነሳው ጭብጥ ኢሕአዴግ ከሚያነሳው ጭብጥ ጋር ስናወዳድር የምናነሳውን ጭብጥ ማወቅ አለብን፡፡ አለበለዚያ በኃይለሥላሴ ጊዜ እንደተደረገው ውሃ በሌለበት ድልድይ እንሰራለን ማለት ይመጣል፡፡ ለምሳሌ ሻኪሶ ለይ የሚወዳደር ሰው ስለ አዶላ ወርቅ ማንሳት አለበት፡፡ ወርቁ ከአፄው ዘመን ጀምሮ ይወጣል፡፡ ግን ወዴት ነው የሚሄደው? ይኽ መነሳት ያለበት ጭብጥ ነው፡፡ ሰዎችንም በተመለከተ ሀገር የሚመሩት፣ አካባቢውን የሚመሩት ምን አይነት ናቸው የሚለውን በግለሰብ ደረጃ ታነሳለህ፡፡ ፖለቲካው ህይወት እንዲኖረው ሁለቱንም ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ጥሩ ምሳሌ ልጥቀስ፡፡ ጠዋትና ማታ መሬት ይሸጣል ይባላል፡፡ በአምቦም፣ በሰባታም፣ በደብረ ብርሃን ወይም... ብትወጣ ካድሬው መሬቱን በጠራራ ፀሐይ እየቸበቸበ ነው፡፡ (ፓርላማም ላይ አንስቸዋለሁ) የሚመለከተው አካል ያውቃል፡፡ ምናልባት ትናንሽ አሳዎችን ወደ እስር ቤት ይወረውር ይሆናል፡፡ ድርጊቱን ግን ኢህአዴግም ሆነ አባላቱ በደንብ ያውቃሉ፡፡ ታዲያ ይህንን ከግለሰብ ጋር ካላገናኘኸው ምን ብለህ ታወራለህ?

***ሪፖርተር፡- ተቃዋሚ ፓርቲዎች (መድረክ) እታች ወርዶ ከሕዝብ ጋር ከመስራት አንፃር ኢህአዴግን ሊወዳደር የሚችልበት አቅም አለው?***

***ዶ/ር መራራ፡-*** መድረክ ሀብት የለውም፡፡ ግን የሕዝብ ሰንሰለቱ ከኢሕአዴግ ይሻላል፡፡ ቢያንስ ቢያንስ መድረክ አፉን ሞልቶ የሕዝብ ብሶት ያነሳል፡፡ ስለ ገበሬዎች ማዳበሪያ ጉዳይ፣ ስለመብራት፣ ስለውሃ፣ ስለመንገድ፣ ስለሰብዓዊ መብት፣ ስለየሕግ የበላይነት ... ያነሳል፡፡ ይኽ ደግሞ ሚሊዮኖችን ያንቀሳቅሳል፡፡ ኢሕአዴግ እንደሚታወቀው አልተሳካለትም፡፡ ፌዴራሊዝም እገነባለሁ እያለ ነው፡፡ መሬት ላይ ግን ባዶ ነው፡፡ ምንም የለም፡፡ ምናልባት ከአፄውና ከደርግ የበለጠ ማዕከላዊ አስተዳደር ነው ያለው፡፡ ከኢሕአዴግ ምርጫ የሀይለሥላሴ ዘመን ምርጫ ይሻላል፡፡ ፊውዳሎች ብቻ እንኳን የሚወዳደሩ ቢሆንም፣ ጠጅ እየገዙ ምረጡኝ በማለትና በመቀስቀስ ከልብ ይቀሰቅሳሉ፣ ያባብላሉ፣ ይለምናሉ ይወዳደራሉ፡፡ አሁን ግን በኢሕአዴግ በኩል የተያዘው ምደባ ነው፡፡
የኑሮ ውድነትን ብንወስድ በ97 ጤፍ 200 ብር ገደማ ነበር፡፡ አሁን እኮ እስከ ሺ ብር ደርሷል፡፡ ሕዝቡ እራሱ ሆዱ ስለሚነግረው ቅስቃሳ አያስፈልገውም፡፡ ኢሕአዴግ አንድ ጊዜ መብላት ያቃተው ሕዝብ ሦስት ጊዜ እንዲበላ አደርጋለሁ ይላል፡፡ ይህ ደግሞ 18 ዓመታት ፈጅቷል፡፡ ሌላ 18 ዓመታት ቢጨመርም ከዚህ ያለፈ የሚሠራ አይመስለኝም፡፡ የኢትዮጵያ ልጆች ዕውቀት ዋጋ ያጣበት ነው፡፡ ኢሕአዴግ ካድሬ ሲመለምል በትምህርት ከማምጣት ይልቅ ስራ ያስቀጥራል እያለ ነው፡፡ ምንም ይሁን ምንም እኛ (መድረክ) ከሕዝቡ ሕይወት ጋር የተሻለ ነገር ስላለን መወዳደር እንችላለን፡፡

***ሪፖርተር፡- በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመድረክ ጋር ከተቀላቀሉ በኋላ የሕዝብ ድጋፍ ርቋቸዋል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እውነት ነው?***

***ዶ/ር መረራ፡-*** ለምን ምርጫውን አይጠብቁም፡፡ ይኽን የሚያወሩት ኢሕአዴግ የሚያሰማራቸው ካድሬዎች ናቸው፡፡ አምቦ፣ ነቀምት፣ ሻሸመኔና ወለጋ ላይ ስብሰባ አካሂደናል፤ ምን ያህል ወጣት እንደነበር በወቅቱ የነበሩትን የመንግሥትም ሆኑ ሌሎች አካላትን መጠየቅ ይሻላል፡፡ ለማንኛውም ከአራት ወራት በኋላ በሚካሄደው ምርጫ እናየዋለን፡፡

***ሪፖርተር፡- በአንድ ወቅት በሰጡት መግለጫ የኦነግ መሪዎች የኦሮሞን ሕዝብ ለመምራት ብቃቱም፣ ዕውቀቱም የላቸውም ብለው ነበር፡፡ በቅርቡ ደግሞ በርካታ የኦነግ ታጣቂዎችና መሪዎች የነበሩ በቁጥጥር ስር ውለው ጋዜጣዊ መግለጫም ሰጥተዋል፡፡ እርስዎ ምን አስተያየት አለዎት?***

***ዶ/ር መረራ፡-*** እውነት ነው፡፡ አሁንም ቢሆን እውነቱ ችሎታውም የላቸውም፡፡ የኦነግ መሪዎች የኦሮሞን ሕዝብ መምራት አይችሉም፡፡ ኢሕአዴግ እኛን ምን አላቸው እያለ እኛን ይከሳል፡፡ እነሱ ሲመጡ ደግሞ ተረክቦ ተንከባክቦ ይቀበላቸዋል፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ ይገርመኛል፡፡ በሕዝብ ላይ ችግር ፈጥረናል፤ ይህንን ስንሰራ ነበር፣ ይህን ስናደርግ ነበር የሚሉትን ሰዎች ኦሕዴድ ለመሆን እስከመጡ ድረስ ወንጀላቸው በሙሉ ይታጠብላቸዋል፡፡ ይህ ትክክል አይደለም፡፡ ወንጀለኞች ናቸው ህዝቡን በድለዋል ካለ፣ እንደዚህ ያለ ነገር ማድረግ የለበትም፡፡ አንድ የኦነግ አመራርም ሆነ አባል እጁን ከሰጠ፣ ኦነግ ፈረሰ፣ የኦነግ መሪዎች እየመጡ ነው ይላል ኢህአዴግ በማግስቱ ደግሞ አባሎቻችንን የኦነግ ደጋፊዎች ናቸው ብሎ ያስራል፡፡ አንድ ሳምንት እንኳን ሳይቆይ፡፡ የኢሕአዴግ ችግር እዚህ ላይ ነው፡፡ የኦነግን መሞት የሚመኘውን ያህል የሚለውና ከመሬት ላይ ያለው አልገናኝ ይለኛል፡፡ የተከፋውም፣ ሌላ ነገር ፍለጋ የሚመጣውም ኦነግ የለም ይላል፡፡ በማግስቱ ደግሞ ኢሕአዴግ የኦነግ አባል ብሎ ሰውን ያስራል፡፡

የኢሕአዴግና ከሱ ጋር የሚመጡት ጨዋታ ሁልጊዜ ይገርመኛል፡፡ ሌላው ኦነግ የኦሮሞ ሕዝብ መብት ብሎ የሚያንቀሳቀሰውን አጀንዳ ኦሕዴድም ሆነ ኢሕአዴግ መፍታት አልቻሉም፡፡ መፍታት እስካልቻሉ ድረስ አሁን ኦነግ ራሱን ለውጦ መጣ፣ ራሱ ኖረ፣ ሌሎች የኦሮሞ ድርጅቶች ተፈጠሩ የመብት ትግሉ አይቀርም፡፡

***ሪፖርተር፡-   ለምንድነው መፍታት ያልቻሉት?***

***ዶ/ር መረራ፡-*** ኢሕአዴግ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አልተንቀሳቀሰም፤ ፌዴራሊዝምን ብንወስድ በእኩልነት እራስህን የምታስተዳድርበት ነው፡፡ ፈረንጆች "ሼርድሩልና ሰልፍሩል" የሚሉት ነገር አለ፡፡ ማዕከላዊ መንግሥት ውስጥ የጋራ አስተዳደር አለ፡፡ ባካባቢ ደግሞ የራስ

(ሰልፍ) አስተዳደር አለ፡፡ ኢሕአዴግ ግን ሁለቱም የለውም፡፡ ዴሞክራሲ አልባ የሆነ ፌዴራሊዝም አይሠራም፡፡ በዓለምም ላይ የለም፡፡ እንዲያውም አደጋ አለው፡፡ ሶቪዬት ሕብረትና ዩጎዝላቪያ የፈረሱት በሁለት ነገር ነው፡፡ አንደኛው ለዓመታት ሲካሄድ የነበረው የውሸት ምርጫ ነው፡፡ ሁለተኛወ የውሸት ፌዴራሊዝም ስለነበረ ነው፡፡ የሶቪዬት ሪፐብሊኮች የሚባሉት እነ ዩክሬን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ነበሩ፡፡ እዛ ድረስ ነበር ነፃነታቸው ግን ባዶና የውሸት ነፃነት ነበር፡፡ ኢሕአዴግም ባዶ ስልጣን ሰጥቷቸው የውሸት ፌዴራሊዝም ነው ያለው፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ኦነግ ኖረም አልኖረ ነፃነቱን ካገኘ በሰላም የማይኖርበት፣ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር አገሩን የማይገነባበት ምክንያት የለም፡፡ ኢሕአዴግ እሱን መፍታት አልቻለም፡፡ ይህን እስካልፈታ ድረስ ኦነግ ሞቷል ብሎ ቢፅፍም ጥቂት የኦነግ አባላት እጅ ቢሰጡም እውነታውና ችግሩ ያው ነው፡፡

***ሪፖርተር፡-  ተቃዋሚዎች እንደ ኬንያና ዚምባብዌ የጥምር መንግሥት መመስረት አለበት ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የማይታሰብና የማይሞከር ነው የሚሉ ወገኖች አሉ እርስዎ ምላሽዎ ምንድነው?***

***ዶ/ር መረራ፡-*** ዶ/ር መረራ እንደዛ ብሎ ቃለ ምልልስ አድርጓል ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ግን ቃለ ምልሱን ልስጥም አልስጥም እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ብዙ ስለሚጠይቁኝ፡፡ አንድ ጊዜ ግን ሽማግሌዎችና ምርጫ ቦርድ ባዘጋጁት ስብሰባ ላይ ተጠይቄ (በሊቀመንበሩ) ስለ ስልጣን መጋራት ሙያዊ ምላሽ ሰጥቻለሁ፡፡ ለማንኛውም ግን ስልጣን መጋራት ሀጢያት የለውም፡፡ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ኢህአዴግ እኔን የሚከሰው ግን እንደ ኬንያ ዚምባቡዌ አመፅ ቀስቅሰን ወዘተ አድርገን የሚል ነው፡፡ ግን እራሱን መመርመር አለበት፡፡ በኬንያም ሆነ በዚምባቡዌ ገዢ ፓርቲዎች የሕዝብ ድምፅ ሰርቀው ለማምለጥ ሲሞክሩ ሕዝቡ ድምፄን ሰርቃችሁ አትሄዱም ብሎ በተፈጠረው ቀውስ እንጅ ተቃዋሚዎች ተሸንፈው አልነበረም፡፡ ኢሕአዴግ መቸም ሙጋቤና ኪባኪ አሸንፈዋል እንደማይል እርግጠኛ ነኝ፡፡ ሁለቱንም ቀውሶች የፈጠሩት ገዢው ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ቀውስ ይፈጥራሉ ብሎ ከሆነ ኢሕአዴግ የሚከሰን በድጋሚ ላረጋግጥ የምወደው በሁለቱም አገሮች ቀውሱን የፈጠረው ገዢው ፓርቲ ነው፡፡

Source: The Reporter Online (January 31, 2010)